**Ung och utsatt för våld i en nära relation - Amhariska**

# ወጣትና በቅርብ ዝምድና መሓል ለነውጥ መዳረግ

በቅርብ ዝምድና መሓል ያለ ነውጥ የተላያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ልጁን ለነውጥ የሚዳርገው ወላጅ ራሱ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ ወንድም ወይም እህት። የቅርብ ዘመድም ሊሆን ይችላል። ምናልባትን አብሮህ/ሽ የሚኖር ሰውም ይሆናል።ነውጥ በዓካል ወይም በኣዕምሮ ላይ ጉዳት ማድረስ፥ እንዲሁም ግብረ ሥጋዊ መድፈር ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል፥ አንድ ሰው

- • በፀያፍ ቃል ከጠራህ/ሽ ወይም መጥፎ ስድብ ከሰደበህ/ሽ ወይም ደካማና መንቻካ እንደሆክ/ሽ እንዲሰማህ/ሽ ካደረገ
- ከገፈተረህ፥ ከመታህ፥ ከቀላህወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ጉዳት ካደረሰብህ/ሽ፥
- ከተቆጣጠረህ ወይም ካገተህ፥ የማትፈልገውን እንድታደርግ ካስገደደህ/ሽ
- ወደ ሌላ ቦታ ሊልክህ/ሽ ወይም ከቤት ሊያባርርህ/ሽ፥ ወይም ቤት ውስጥ ሊቆልፍብህ/ሽ የሚዝት ከሆነ፥
- ለግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚያስገድድህ/ሽ ከሆነ
- የቤተሰብን ሥም መጠበቅ በሚል ሰበብ የተወሰኑ ደንቦችን እንድታከብር ካስገደደህ/ሽ
- በሌላ የቤተሰብ አባል ላይነውጥ የሚጠቀም ከሆነ

**ጥበቃና ድጋፍ የማግኘት መብት ኣለህ/ሽ**

አንድ ሰው ለነውጥ ሲዳረግ መጨነቁና ማዘኑ የተለመደ ነው። ስለዚህ ሊሰማህ/ሽና ሊረዳህ/ሽ ከሚፈልግ ሰው ጋር መነጋገር አስፈላጊ ነው። አንድ ከ18 ዓመት ዕድሜ በታች ያለ/ያለች ወጣት ለነውጥ ተዳርጎ/ጋ ከተገኘ/ች ሁሌም በኃላፊነት የሚጠየቀው ዐዋቂው ሰው ነው። ከማሕበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ዘንድ የድጋፍ፥ የጥበቃና የሌላም ተግባራዊ ነገሮች እርዳታ ታገኛለህ/ሽ።

**የሚከተሉትን ድጋፎች ታገኛለህ/ሽ**

- ውይይታዊ ድጋፍ
- ጥበቃና ግዚያዊ መኖሪያ
- ለግጭቱ መፍትኄ ለመሻት ከቤተሰቦችህ ጋር ውይይታዊ ድጋፍ

እንድንረዳህ/ሽ አግኘን/ አግኚን። ማንነትህ/ሽን ማሳወቅ ኣይኖርብህም/ሽም፥ ስምህን/ሽን ወይም የምትኖርበትን ቦታ መግልጽ የለብህም/ሽም።

ለኣስቸኳይ ጊዜ ሁሌም 112 ደውል/ ደውዪ።

**ከእነዚህ ጋር ግንኙነት አድርግ/ጊ፥**

- **ሥራው/ኀላፊነቱ:** Barn och ungdomsenhetens mottagningsgrupp
- **ስልክ ቁጥር:** 08-58169000
- **ድረገጽ:** www.upplands-bro.se
- **ኣድራሻ:** Furuhällsplan 1, Kungsängen

**Barn som upplever våld i en nära relation - Amhariska**

# በቅርብ ዝምድና መሓል ለነውጥ የሚዳረግ ልጅ

አንድ ልጅ ለሚከተሉት ሁኔታዎች ሲዳረግ፥ ነውጥ ተፈጸመበት ማለት ነው።

- ለነውጥ መጋለጥ (ከምት፥ ግፍትሪያ፥ ግብረ ሥጋዊ መደፈር፥ መዋረድ እስከ ስነልቦናዊ ድሽቀት)
- ነውጥ ሲተገበር ማየት ወይም መስማት፥
- የነውጥ ምልክቶችን ማየት (ለምሳሌ ገላ ላይ ሰማያዊ ምልክት፥ የተሰባበሩ ዕቃዎች፥ ፍርኀት)
- ቤት ውስጥ ያለው የጭንቀት ድባብ ሲሰማው።

ኣሳዳጊዎች ባይመስላቸው፥ አብዛኛዎቹ ልጆች ቤተሰብ ውስጥ የሚካሔደውን ነገር በደንብ ይገነዘባሉ። ልጆች የውስጥ ስሜታቸውን ኣይገልጹም እንጂ ያቀረቡት ሰው ሲከፋው ይታወቃቸዋል። በመካያው ልጆች ሲከፋቸው ወይም ሲጨነቁ በሚጫወቱበት ጊዜ ወይም በባኅሪያቸው ላይ በሚታይ ለውጥ ያስታውቃሉ።

**የኣሳስቦኛል ማመልከቻ ያስገቡ**

አንድ ልጅ ያልተመቸው መስሎ ከታየት፥ ለማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የአሳስቦኛል ማመልከቻ ያስገቡ። ለማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ውይይታዊ ድጋፍ ከመስጠት ኣልፎ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

አንዳንድ የሙያ ተቋሞች የአሳስቦኛል ማመልከቻ የማስገባት ሕጋዊ ግዴታ ኣለባቸው። ይህ ለምሳሌ ያህል ት/ቤትን፥ የጤና ተቋማትንና ፖሊስን ይመለከታል።

**ለነውጥ የሚዳረግ ልጅ ድጋፍ**

ልጁና ኣሳዳጊዎቹ ከማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ድጋፍ ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ

- ውይይታዊ ድጋፍ
- የልጆች ቡድን ውስጥ መሳተፍ
- የወላጅ ሚናን አስመልክቶ ለልጁ ሲባል የሚደረግ ድጋፍ
- አንድ የሚገናኙት ሰው ወይም ቤተሰብ
- ጉዳዩ አስቸኳይ ከሆነ ሌላ እርምጃ፥ ለምሳሌ ግዚያዊ መቆያ ቤት።

ለአስቸኳይ ጊዜ ሁሌም 112 ይደውሉ።

**ከእነዚህ ጋር ግንኙነት ያድርጉ፥**

- **ሥራው/ኀላፊነቱ:** Barn och ungdomsenhetens mottagningsgrupp
- **ስልክ ቁጥር:** 08-58169000
- **ድረገጽ:** www.upplands-bro.se
- **ኣድራሻ:** Furuhällsplan 1, Kungsängen